# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

## Catering and Tourism Training Institute

ቅጽ 1 ቁ ጥር 2 ሐምሌ 2011 ዓ.ም

በህዝብና ዓለማቀፍ ግንኙነት ዳ/ት እየተዘጋጀ የሚቀርብ

ስልክ 0115308126
ፖስታ ሳ.ቁ 4350
Www.cttiedu.org

## የሱፐር ቪዥን ቡድን የዳሰሳ ውጤት ለማኔጅመንት አባላት ቀረበ

የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም በበላይ አመራሩ የተዋቀረና በአራት ተከፍሎ የስራ ክፍሎችን ሲገመግም የነበረው የሱፐር ቪዥን ቡድን የቀረበው የዳሰሳ ውጤት ለማኔጅመንት አባላት ቀረበ።

የሱፐር ቪዥን ቡድን አባላት 16 የሥራ ክፍሎችን የዳሰሱ ሲሆን በቀረቡት የሥራ ክፍሎች እንደየ ዘርፋቸው ተመሳሳይ የመለኪያ መስፈርቶች የተቀመጡ ሲሆን በአካዳሚክ ክፍሎች ከትምህርት ጥራትና ከተደራሽነት አንፃር ፣ ከዕቅድና ሪፖርት አቀራረብ ከክፍለጊዜ ብክነትና መረጃ አያያዝ፣የዕቅድና ሪፖርት ማካተትን በዋናነት እንደ መስፈርት የተያዙ ናቸው። በአስተዳደር ዘርፉም ዕቅድና ሪፖርት ዝግጅት የመልካም አስተዳደር ዕቅድ፣መረጃ አያያዝ እና ሌሎች በሱፐር ቪዥን ቡድኑ ከክፍል ኃላፊዎች ጋር በመሆን የሥራ ክፍሎችን ዳሷል። በዚህ የመጀመሪያ ሪፖርት ለማኔጅመንት አባላቱ

→ ወደገ ጽ 2

## የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትቱ የ2011 ዓ.ም ሰልጣኞቹን አስመረቀ

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በዲግሪና በደረጃ በተለያዩ ሙያዎች በቀንና በማታ መርሃግብር ያሰለጠናቸውን 809 ሰልጣኞችን አስመረቀ።

በዕለቱ ለተማራቂዎች የመግቢያ ንግግር ያደረጉት ክብርት ወ/ሮ ቡዝነሽ መሰረት የባህል ቱሪዝምና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ ዘርፉ በፍጥነት እያደገ የሚሄድና ተለዋዋጭ በመሆኑ በዘርፉ የሰለጠነና ብቃት ያለው የሰው ሃይል ማፍራት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው ተመራቂዎች በሚሰሩበት ቦታ ሁሉ የሀገርን ጥቅም በማስቀደም ኃላፊነታቸውን መወጣት





*ክብርት ወ/ሮ ብዙነሽ መሰረት*

እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

በተጨማሪም የዛሬ ተመራቂዎች የሰለጠናችሁበትን ሙያ ማክበር፣ማስከበር እንግዶችን ማስተናገድ የሃገርንና የህዝብን ክብር መጠበቅ፣ ታማኝነት በእጅጉ ከተመራቂው እንደሚጠበቅ →

## የዳሰሳ ውጤት

በሱፐርቪዥን አባላት የቀረበው ገንቢ ሃሳብ ነው፤ አንዳንዱም አይገልፅንም ያሉ፤ መታየት ያለበት አልታየም ያሉም ጭምር ሃሳብ ሰጥተው ውይይት ተደርጎበታል፡፡

የተቋማችን ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ የሰው ሃይል ዕጥረት የቢሮ ጥበት እና የግዢ መጓተት በአብዛኛው የስራ ክፍሎች የተዳሰሰ መሆኑን ገልጠው፤ በሱፐርቪዥን ቡድኑ የቀረበውን ሪፖርት ለመማማሪያነት እንድንጠቀምበት ከቢሮ ጥበት ጋር የተያያዘውን ችግር የካይዘን ኢንስቲትዩት ጋር በመነጋገር ላይ እንዳሉ እና በአጭር ጊዜ የተወሰኑ ቢሮዎችን ነፃ ማድረግ እንደሚያስችል ገልፀዋል፡፡

### ሀገር አቀፍ የአረንጓዴ አሻራ ቀን

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰራተኞች፣ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚዲያ ፎረም አባላትና ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን በገላን ችግኝ ተከላ አካሄዱ፡፡ ዛፎች የአካባቢን ደህንነት ከመጠበቃቸው፣ የአየር ንብረትን ከሙቀትና ከብክለት ከመታደጋቸው ባሻገር ለዓለም ኢኮኖሚ ዋልታ ናቸው፡፡ "ሐምሌ 22 በሀገራችን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠውና ኢትዮጵያውያን በዘር፣ በሀይማኖት፣ በእድሜ፣ በፆታ ወይም በሌላ ሳይከፋፈሉ በአንድነት የነገዋን ኢትዮጵያ ለመገንባት አረንጓዴ አሻራቸውን የሚያስቀምጡበት ነው፡፡ ሀገሪቱ ለዓለም ሙቀት መጨመር ምክንያት ሳትሆን ተግባራዊ መፍትሄ በመስጠት ቀዳሚ ሀገር መሆንዋን ኢትዮጵያውያን የሚያስመሰክሩበት ነው፡፡ በችግኝ ተከላ ፕሮግራሙ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚዲያ ፎረም አባላት እንዲሁም የባህለና ቱሪዝም ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡

## ምረቃ

ሚንስትር ዴታዋ ተናግረዋል፡፡ ***እንዲሁም ሁሉም ሙያ ክብር ቢሆንም እናንተ የሰለጠናችሁበት ሙያ ደግሞ እጅጉን ክቡር ስለሆነ የደከመው፣የራበው፣ መዝናናት ያማረው እንግዳ ከፊታችሁ ይቀርባል፤ ይህን እንግዳ በትንሹ በፈገግታና በክብር ማስተናገድ ይጠበቅባችኋል፤ ሌላው አንድ ቱሪስት የአገሪቱን ባህልና ታሪክ፣የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅርስ ለማየት ረጅም ርቀት ተጉዞ ሲመጣ፤ እናንተ ያላወቃችሁትን ባህልና ታሪክ ለሌላው ለመንገር አትችሉም፡፡ ስለዚህ ባህልና ታሪክ ማወቅና መጠበቅን፣ በራስ ታሪክ መኩራትን ከናንተ ይጠበቃል፡፡ ይህ አደራ ደግሞ ዛሬ የምትሸከሙት በሥራ ላይ እንዲተገብሩት በማለት የገለጹት ወ/ሮ ብዙነሽ ቃል እንዲገቡ ጭምር አሳስባለሁ***

ክብርት ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የማሰልጠኛ ማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው የሀገራችንን የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ ለማሳደግ ኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልፀው ተቋሙ ላለፉት 50 ዓመታት በርካታ ባለሙያዎችን ያፈራ ፤ በአሁኑ ጊዜ ከመላው የሃገሪቱ ክፍል ኢንዲስትሪው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሃይል እያቀረበ የሚገኝና በቱሪዝምና በሆቴል ዘርፍ አንቱ የተባሉ አንጋፋ ባለሙያዎችንም ያፈራ መሆኑን

## USAID Representatives at Catering and Tourism Training Institute!

Representatives of the USAID and Advisor to Minister, at FDRE Ministry of Culture and Tourism Mr. Yohannes Tilahun had a discussion with the General Director of Catering and Tourism Training Institute Mrs. Aster Dawit at the meeting hall of the institution.

The discussion was held on how to work in the future for the human development of hospitality and tourism industry of



the institute and they looked at

on how trainees are practicing.

The discussion has end with a visit for the different shops of the institute and they looked at on how trainees are practicing.



## ምረቃ





*ወ/ሮ አስቴር ዳዊት*

ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ እንዲገባና በዘርፉ በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ብቃት ያለው ስልጠና እንዲሰጥ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ ጥረት እየተደረጉ መሆኑ የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ጠቁመዋል።

ተመራቂዎች በንድፈ ሃሳብና በተግባር የቀሰሙትን እውቀት ወደ ተግባር በመለወጥ የሃገራችንን በጎ ገጽታ እንዲገነቡ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን እና በሚኖራቸው የህይወት ጉዞ መልካም ስነምግባር ተላብሰው እንዲጓዙ የአደራ መልዕክት አስተላልፈዋል። ።

# አረንጓዴ አሻራ



በዓለማችን የካርበን ልቀትን ለመቀነስ በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የተለያዩ መድረኮች ተፈጥረው ውይይት ስካሄድ ቆይቷል፡፡

ኢትዮጵያም በዚህ መድረኮች አፍሪካን በመወከል ድምጻችንን ለዓለም ማህበረሰብ አሰምታለች፡፡ ይህንን የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንገዓዴ ኢኮኖሚ በላቀ ደረጃ ለመፈጸም እንዲሁም ከዘርፉ የቱሪዝም ሴክተር ለማሳደግ ከፍተኛ ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በሃገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ አገር አቀፍ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ሐምሌ 22 2011 ዓ.ም በአንድ ጀምበር 200 ሚሊየን ለመትከል ታቅዶ ከ350 ሚሊየን ችግኝ በላይ እንደተተከለ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ይህ ችግኝ ተከላው ሃገራችን ከልዩነት ይልቅ በአንድነት በዘር፣ በሃይማኖትና በጾታ ሳይከፋፈሉ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት በነቂስ ወጥቶ አረንጓዴ አሻራቸውን ያሰቀመጡበት ልዩ ቀን ነው፡፡

ችግኝ ተከላው የአየር ንብረት ለውጥን ከመጠበቁ ባሻገር ሃገራችን ከዚህ በፊት በዓለም የሚትታወቅበትን በመልካም ለመቀየርም ምቹ አጋጣሚ ሆኗል፡፡

ይህም በዓለም ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያላት ህንድ 66 ሚሊየን ችግኝ በመትከል ቀዳሚ የነበረችበትን ክብረ ወሰን በመስበር በዓለም ሚዲያዎች ኢትዮጵያ እንድትታወቅ ያደረገ በመሆኑ ወደ ሃገራችን የሚመጡ የቱሪስት ቁጥር ከፍ ያደርጋል ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡

በዚህ የችግኝ ተከላ ቀን የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰራተኞች፣ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚዲያ ፎረም አባላት፣ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን በገላን አከባቢ ችግኝ ተከላ ተከናውኗል፡፡ በሰራተኛው ይታይ የነበረው ተነሳሽነት ይህችን ቀን በህይወት አጋጣሚ አንድ ጊዜ ከሚገኙ አጋጣሚዎች ጋር በማገናኘት ችግኝ ለመትከል፣ ጉድ ጓድ ለመቆፈር የነበረው ጉጉት ደስ የሚል ነበር፡፡

እርግጥ የችግኝ እጥረት ገጥሞን እጃቸው ጭቃ ሳይነካው በሃዘን የተመለሱትንም አስተውለናል፡፡

ዋናው የሥራው አካል ሆነን በታው ላይ መገኘታችን ፤አንድነቱ በአገር ጉዳይ እንዲህ በፍቅር ስንታዘዝ ማየት መልካም አጋጣሚ በመሆኑ የዚህ ሃሳብ ጠንሳሽና አስፈፃሚ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን በእጅጉ ምስጋና ይገባዎታል፡፡

